*Amarinja*

**የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ**
በ1948 ተጻፈ

የሰው ልጅ ሁሉ ሲወለድ ነጻና ብክብርና ብመብትም እኩልነት ያለው ነው። በተፈጥሮ የማስተዋልና ሕሊና ስላለው አንዱ ሌላውን በወንድማማችነት መንፈስ መመልከት ይገባዋል።

እያንዳንዱ ሰው በሰላምና በደህንነት የመኖር መብቱ የተጠበቀ ነው።

ማንኛውም ሰው ከባድ ስቃይ ክሚያወርድ ጭካነ የሞላው ኢሰብአዊ ተግባር አይፈጸምበትም፥ ወይንም ሰብአዊ ክብሩን የሚነካ አያያዝ አይፈጸምበትም።

አካለ መጠን የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር በዜግነት ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይወሰኑ ጋብቻን የመፈጸምና ቤተሰብን የመመስረት መብት አላቸው። ጋብቻ በመፈጸም በጋብቻ ጊዜና ጋብቻ በሚፈርስበትም ጊዜ እኩል መብት አላቸው።

እያንዳንዱ ሰው የሃሳብ የሂሊናና የሃይማኖት ነጻነት የማግኘት መብት አለው። ይህም መብት ሃይማኖቱን ወይም እምነቱን የመለወጥ መብቱን ያጠቃልላል።

እያንዳንዱ ሰው የመስራት የስራ ነጻ ምርጫና ለስራም ትክክለኛና ተሰማሚ የአሰራር ሁኔታዎችና ስራም እንዳያጣ ለሚያስገኝ ዋስትና መብት አለው።

እያንዳንዱ ሰው ትምህርት የማግኘት መብት አለው። ትምህርት ለእያንዳንዱ ሰው ሁኔታ ማሻሻያና ለሰብአዊ መብቶችም መሰረታዊ ነጻነቶች ክብር ማዳበርያ የሚውል መሆን አለበት።

እያንዳንዱ ሰው ህብረተሰብአዊ ግዴታ አለበት።

**በሴቶች ላይ ለሚፈጸም ጭቆና ለማስወገድ የወጣ ድንጋጌ**
በ1979 የተጻፈ

ሴቶች በምርጫ ጊዜ ድመጽ ለመስጠት፥ ህዝባዊ ብሆኑ ቦታዎች ቦታ ለማግኘት፥ እንዲሁም ብሄራዊና ዓለም አቀፋዊ ቦታ ላይ ለመሳተፍ እኩል መብት አላቸው።

በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን ማህበራዊ አመለካከት ለመለወጥ እርምጃዎች መወሰድ ይገባቸዋል። ሁዋላ ቀር ባህልና ልምድ ላይ ተመርኩዞ ሴቶችን ዝቅ የሚያደርግ ወይም ለወንዶች ብቻ መብት የሚሰጥ አመለካከት መወገድ አለበት።

ሴቶች ዜግነታቸውን እራሳቸው የመምረጥና የመወሰን መብት አላቸው። ትዳር በሚመሰርቱበት ወቅት ላይ ተገደው የባላቸውን ዜግነት መውሰድ የለባቸውም።

ለጆች በቀጥታ የአባታቸውን ዜግነት ብቻ መውሰድ የለባቸውም።

ሴቶች በአጠቃላይ ትምህርትና በከፍተኛ ትምህርት የመመርቅና ስራ የማግኘት ዕድል እኩል መብት አላቸው።

በሁዋለ ቀር ባህል ላይ ተመርኩዞ በትምህርትና በስራ ላይ የጾታ ልዩነት ለሚያመጡ ነገሮች የሚከላከል ስራ መሰራት አለበት። መማርያ መጻህፍቶች ሁዋለ ቀረ ባህል ላይ ለተመረኮዘ የጾታ ልዩነቶች ቦታ መሰጠት የለበትም። በአንጻሩ ትምህርትና ስራ ሲመረጥ ጾታ ሚና የሌለበት አሰራር ማበረታታት ይገባል።

ሴቶች ስራ በነጻ ፍላጎታቸው እንዲመርጡ፥ እኩል ደሞዝና ህብረተሰበዊ ዋሶች፥ የስራና ቤተሰብአዊ ዋስ የማግኘት መብት እንዲሁም ከባንክ ሆነ ከሌሎች አበዳሪ ድርጅቶች የመበደር መብት አላቸው።

ሴቶች በነፍሰጹርነት ወይም በእናትነት ምክንያት ከስራ መባረር የለባቸውም።

ስራና ተዳር ተሰማምቶ እንዲሄድ እንዲሁም የሴቶች ህዝባዊ ተሳትፎ እንዲጠንክር ህብረተሰቡ አመቺ ሁኔታዎች መፍጠር አለበት።

ሴቶች የጤናና የህክምና ቦታዎች ለማግኘት ዕድል እንዲኖራቸው እንዲሁም ልጅ የማፍራትን ነገር በተመለከተ እራሳቸው መወሰን አለባችው።

ሴቶች ብህግና በፍርድ ቤት እኩል መብት አላቸው። የንበረት ባለቤትነት መብታቸውም መነጠቅ የለበትም።

ሴቶች ወደ ፈለጉበት ቦታ የመንቀሳቀስና እፈለጉበት ቦታ የመኖር መብት አላቸው።

ሴቶች ትዳር ለመመስረት፥ ስራ ለመምረጥ፥ ትዳር በሚመሰርቱበት ወቅት ክፍላጎታቸው ውጭ መሆን እንደሌለበት እንዲሁም ፍትህን በተመለከተ እኩል መብት አላቸው።

ሴቶች ልጆች ለማሳደግ፥ ለመከናከን ሆነ ለሞግዚትነት እኩል መብት አላቸው።

ሴቶች የቤተሰብ ስም የመምረጥ መብት አላቸው።

**የህጻናቶች መብት ድንጋጌ**
በ1989 የተጻፈ

በሲዊድን ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሁሉ ህጻን በመባል ይታወቃል።

ህጻናቶችን በተመልከተ ጉዳይ ሁሉ ለነሱ አመቺ የሆነው ነገር ቅድምያ ይኖረዋል። ህጻናቶች የመኖር መብት አላቸው።

ህጻናቶች እንደተወለዱ መመዝገብ ይኖርባቸዋል። ስም የማግኘትና የዜግነት መብት እንዲሁም የሚቻል ከሆነ ወላጆቻቸው ማን እንደሆኑ የማወቅ መብት አላቸው።

ህጻናቶች ያለፍላጎታቸው ከወላጆቻቸው መነጠል የለባቸውም።

ለህጻናቶች አመቺ ሆኖ ከተገኘ ከወላጆቻቸው መነጠል ይችላሉ። ለምሳሌ ጥቃት ቢደርስባቸው ወይም ጥሩ አስተዳደግ ሳይደረግላቸው ቢቀር ወይም ወላጆቻቸው ተለያይተው የሚኖሩ ከሆነ ህጻናቶች የት መኖር እንደሚኖርባቸወ መወሰን ያስፈልጋል።

ህጻናቶች ወላጆቻቸው ተለያይተው የሚኖሩ ከሆነና ይህም ከህጻናቶቹ ጥቅም ጋር የማይጋጭ ሆኖ ከተገኘ ከወላጆቻቸወ ጋር የሚገናኙበትን መንገድ መፈለግ።

ህጻናቶችን በህገወጥ መንገድ መጥለፍና በውጭ አገር ማቆየት አይቻልም።

ህጻናቶች ሃሳብቸወን የመግለጽ መብት ሰላላቸወ እነሱን በተመለከተ ጉዳይ ላይ ሃሳባቸውን ያለምንም ጫና መግለጽ መቻል አለባቸው። ዕድሜአቸውንና ብስለታቸውን ግን ግምት ወስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

የህጻናቶች በነጻ የማሰብ መብትና እንዲሁም የሂሊናና የሃይማኖት መብታቸው መከበር አለበት።

ህጻናቶች በግላዊ ሆነ ቤተሰብዊ ኑሮአቸው ህጋዊ ሆነ ህገወጥ ጫና መደረግ የለበትም።

ለህጻናቶች ከአካላዊ ሆነ ሰነ አእምሮአዊ ጥቃት፥ ጉዳት ወይም ጥቃት ወይም መጥፎ አስተዳደግ ወይም መጥፎ አያያዝ ወይም ከግብረሰጋዊ ጥቃት ሆነ ጭቆና በሚከላከልላቸው ህግ በኩል ህብረተሰበዊና አስተዳደራዊ እርምጃ መወሰድ አለበት።

ለጊዜው ከወላጆቻቸወ የተለዩ ህጻናቶች ከህብረተሰቡ አስፈላጊ ክንክናን እርዳታ የማግኘት መብት አላቸው። በአፈጻጸሙ ላይ የህጻናቶቹን ብሄር፥ ሃይማኖት፥ ባህልና ቃንቃን ግምት ወስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

አካላዊ ሆነ ሰነአእምሮአዊ ጉድለት የደረሰባቸው ህጻናቶች ትርጉም ያለውና የተማላ ህይወት የማግኝት መብት አላቸው።

ህጻናቶች ጤናቸወን ከሚጎዳ ሁዋላ ቀረ ባህል መጋልጥ የለባቸወም።

ህጻናቶች ስብእናቸውን ማለት አካላዊና ሰነአእምሮአዊ ችሎታቸወን የሚያዳብር ትምህርት የማግኝት መብት አላቸው። የሚሰጠው ትምህርት ህጻናቶች ወላጆቻቸውን ለማክበር የሚረዳ፥ የህጻናቶችን ባህል፥ ማንነት፥ ቃንቃና ከበረቶች ይሚያጎለብት፥ ህጻናቶቹ የሚኖሩበትን ወይም የመጡበትን ባህልና ክብር የሚያጎለብት እንዲሁም ከህጻናቶቹ የተለዩ ባህሎች ላይ አክብሮት እንዲኖራቸው የሚያግዝ መሆን አለበት።

ህጻናቶች የእረፍትና ትርፍ ጊዜ የማግኘት መብትና ከእድሜአቸው ጋር የሚመጣጠን የትርፍ ጊዜ ማሳለፍያ ቦታዎች የማግኘት መብት አላቸው።

ህጻናቶችን የሚጎዱ ጠለፋና መሸጥ የተከለከለ ነው።

*"ማንኛውም ባህል፥ ሃይማኖት ሆነ ክብር ሴቶችን ለመጨቆን ምክንያት መሆን የለበትም። ማንኛውም ባህል፥ ሃይማኖት ሆነ ክብር አንዲት ልጅአገረድ ግላዊ ሂወትዋን እንዳትመራ ወይም መወሰን ያለባትን ወሳኔዎች እንዳትወስን ምክንያት መሆን የለበትም።" ሙና ሳሊን*

***Amarinja***



ከተባበሩት መንግስታት የተውጣጡ
ሶስት ሰነዶች*

- የስብአዊ መብቶች ድንጋጌ
- በሴቶች ላይ ለሚፈጸም ጭቆና ለማስወገድ የወጣ ድንጋጌ
- የህጻናቶች መብት ድንጋጌ

የጽሁፉ አዘጋጅ ሲሞን ሊንድስተን
Länsstyrelsen Västra Götalands län

**Översättning:**

LÄNSSTYRELSEN
VÄSTRA GÖTALANDS LÄN

* För texterna i sin helhet, se www.humanrights.se